# ሳምንታዊ የክፍያ ጥያቄዎች ተገልፀዋል

| **ምን እንደሚል** | **ምን ማለት እንደሆነ** |
|---|---|
| ለዚህ ሳምንት የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን መቀበል ይፈልጋሉ? | እንደአስፈላጊነቱ የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ መውሰድ ይችላሉ:- ሙሉ ሳምንታት፣ ከፊል ሳምንታት፣ ወይም የተወሰኑ ሳምንታትን ማለፍ ይችላሉ።<br>• ለዚህ ሳምንት ጥቅማጥቅሞችን ለመጠየቅ ወይም ይህ የመጀመሪያ ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎ ከሆነ እና የእረፍት ፈቃድዎ የመጠባበቂያ ሳምንት የሚፈልግ ከሆነ **አዎ** የሚለውን ይምረጡ።<br>• ጥቅማ ጥቅሞችን መጠየቅ የማይፈልጉ ከሆነ **አይ** የሚለውን ይምረጡ። ለዚህ ሳምንት ክፍያ አይቀበሉም። |
| ለዚህ ሳምንት የስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞችን ተቀብለዋል ወይም ይቀበላሉ? | የስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች የሚሰጡት ሥራ አጥ ለሆኑ ወይም በከፊል ተቀጥረው ለሚሠሩ ሰዎች ናቸው። ይህ ከሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ የተለየ ፕሮግራም ነው።<br><br>ለዚህ ሳምንት የስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞችን ተቀብለው ከሆነ ወይም የሚቀበሉ ከሆነ **አዎ** የሚለውን ይምረጡ።<br>• ለተመሳሳይ ሳምንት ከስራ አጥነት እና ከሚከፈልበት የእረፈት ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን መቀበል ህገወጥ ነው።<br>• የትኛውን ፕሮግራም መጠቀም እንዳለብዎት መምረጥ የእርስዎ ኃላፊነት ነው። |
| በሥራ ቦታ ላይ በደረሰብዎት ጉዳት ምክንያት የሰራተኞች ካሳ ተቀብለዋል ወይስ ይቀበላሉ? | የሰራተኞች ካሳ የሚሰጠው በሥራ ቦታ ላይ በደረሰብዎት ጉዳት ምክንያት እርስዎ ሥራ መስራት በማይችሉበት ጊዜ ነው። የሚከፈለው በ Labor & Industries ወይም በአሰሪዎ የግል መድን ሰጪ ነው።<br><br>ለዚህ ሳምንት ለሰራተኞች የሚከፈለውን ካሳ ተቀብለው ከሆነ ወይም የሚቀበሉ ከሆነ **አዎ** የሚለውን ይምረጡ።<br>• ለተመሳሳይ ሳምንት ከሰራተኞች የሚከፈለውን ካሳ እና ከሚከፈልበት የእረፈት ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን መቀበል ህገወጥ ነው።<br>• የትኛውን ፕሮግራም መጠቀም እንዳለብዎት መምረጥ የእርስዎ ኃላፊነት ነው።<br><br>የአጭር ጊዜ የአካል ጉዳተኝነት ድጋፍ ለሰራተኞች ከሚከፈል ካሳ የተለየ ነው። የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ መቀበል በእነዚያ ጥቅማጥቅሞች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ለማየት የአጭር ጊዜ የአካል ጉዳተኝነት እቅድዎን ይፈትሹ። |
| በዚህ ሳምንት ማንኛውንም ሰዓት ስራ ሰርተዋል? | የግል ስራን ጨምሮ፣ በዚህ ሳምንት ውስጥ ለማንኛውም አሰሪ ስራ ሰርተው ከሆነ፣ ምንም እንኳን እርስዎ የእረፍት ፈቃድ የምወስዱበት አሰሪ ባይሆንም፣ **አዎ** የሚለውን ይምረጡ። |
| ስንትያህል ሰዓታትን ሰርተዋል? | የግል ስራን ጨምሮ፣ በዚህ ሳምንት ውስጥ ለሁሉም አሰሪዎች፣ ምንም እንኳን እርስዎ የእረፍት ፈቃድ የምወስዱበት አሰሪ ባይሆንም፣ የሰሩትን አጠቃላይ የሰዓት ብዛት ያስገቡ። |

## ሳምንታዊ የክፍያ ጥያቄዎች ተገልፀዋል

| | |
|---|---|
| | • የእርስዎን ሰዓታት ወደ ሙሉ ቁጥር ያጠጋጉ።<br>• በተፈቀደልዎ የእረፍት ፈቃድ ቀናት ውስጥ የተሰሩ ሰዓታትን ብቻ ያካትቱ። |
| በተከታታይ ቢያንስ 8 የስራ ሰዓታት አምልጦዎታል? | በዚህ ሳምንት በተከታታይ ቢያንስ 8 የስራ ሰዓታት አምልጦዎት ከሆነ **አዎ** የሚለውን ይምረጡ፣ ለምሳሌ፦<br>• ሙሉ የ8-ሰዓት ፈረቃ፣ ወይም<br>• የአንድ ፈረቃ የመጨረሻዎቹ 4 ሰዓታት እና የቀጣዩ ፈረቃ የመጀመሪያ 4 ሰዓታት፣ ወይም<br>• በተከታታይ ሁለት የ 4-ሰዓት ፈረቃዎች። |
| እንደ የእረፍት ጊዜ፣ የህመም ጊዜ ወይም የበዓል ጊዜ ክፍያ ያለ ማንኛውንም የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ተጠቅመዋል? | • እንደ የእረፍት ጊዜ፣ የህመም ጊዜ፣ የበዓል ጊዜ ክፍያ ወይም ተጨማሪ ጥቅማጥቅም ያልሆነ ሌላ የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ተጠቅመው ከሆነ **አዎ** የሚለውን ይምረጡ።<br>• ማንኛውም የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ካልተጠቀሙ፣ ወይም የእርስዎ የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ተጨማሪ ጥቅማጥቅም ከሆነ **አይ** የሚለውን ይምረጡ።<br>አንዳንድ አሰሪዎች ሰራተኞች ተጨማሪ የሆነ የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ወይም ከመደበኛው የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞች በተጨማሪ እንዲጠቀሙ ይፈቅዳሉ። የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜዎ ተጨማሪ እንደሆነ ለማወቅ ከአሰሪዎ ዘንድ ያረጋግጡ። |
| ስንት የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ፣ የህመም ጊዜ ወይም የበዓል ጊዜ ክፍያ ሰዓታትን ተጠቅመዋል? | በዚህ ሳምንት የተጠቀሙበትን የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ፣ የህመም ጊዜ፣ የበዓል ጊዜ ክፍያ ወይም ሌላ የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ አጠቃላይ የሰዓታት ብዛት ያስገቡ።<br>• የእርስዎን ሰዓታት ወደ ሙሉ ቁጥር ያጠጋጉ።<br>• በተፈቀደልዎ የእረፍት ፈቃድ ቀናት ውስጥ የተጠቀሙ ሰዓታትን ብቻ ያካትቱ።<br>• በአሰሪዎ ተጨማሪ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሰዓታትን አያካትቱ። |

## ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች

*ሳምንታዊ የክፍያ ጥያቄ ምንድን ነው?*

ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎች የእርስዎ የእረፍት ፈቃድ ከጀመረ በኋላ ክፍያ እንዴት እንደሚደርስዎት የሚያሳዩ ናቸው። በእረፍት ጊዜዎ ወቅት፣ በየሳምንቱ ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄ ያቀርባሉ። ያለማቋረጥ የእረፍት ፈቃድ እየወሰዱ ከሆነ እና ለአንድ ሳምንት የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞችን መቀበል ካልፈለጉ፣ አሁንም ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ አለብዎት።

የወረቀት ማመልከቻ በመጠቀም የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ለደንበኛ እንክብካቤ ቡድን በስልክ ቁጥር 833-717-2273 በመደወል ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችን ያቀርባሉ። ኦንላይ በመጠቀም የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ወደ የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ መለያዎ በመግባት ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችዎን ያቅርቡ።

# ሳምንታዊ የክፍያ ጥያቄዎች ተገልፀዋል

*ሳምንታዊ የክፍያ ጥያቄዬን የማስመዘግበው መቼ ነው?*

ምንም እንኳን በዚያ ሳምንት የእረፍት ፈቃድ ባይወስዱም፣ በየሳምንቱ ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ አለብዎት። የአንድ ሳምንት የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ እሁድ ከጀመረ እና በሚቀጥለው ቅዳሜ የሚጠናቀቅ ከሆነ፣ ሳምንቱ እስኪያልቅ ድረስ ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም። ይህም ማለት ለባለፈው ሳምንት እሁድ ላይ ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

**ማመልከቻዎ እንደፀደቀ ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችዎን ማስገባት ይጀምሩ።**

*የመጠባበቂያ ሳምንት ምንድን ነው?*

እራስዎን ለመንከባከብ የህክምና እረፍት የሚወስዱ ወይም የቤተሰብ አባል ለመንከባከብ የቤተሰብ እረፍት የሚወስዱ ከሆነ የተፈቀደ እረፍትዎ የመጀመሪያው ሳምንት የመጠባበቂያ ሳምንት ነው። ለዚህ ሳምንት ክፍያ አይከፈልዎትም፣ ሆኖም አሁንም ሳምንታዊ የክፍያ ጥያቄዎን ማስመዝገብ አለብዎ።

ከልጅ ወለድ ለማገገም፣ ከአዲስ ልጅ ጋር ያለዎትን ግንኙነት ለማጠንከር ሲባል፣ ወይም ለወታደራዊ ዝግጅቶች ሲባል የእረፍት ፈቃድ እየወሰዱ ከሆነ የመጠባበቂያ ሳምንት የሉዎትም።

*ከክፍያ ጋር በሚሰጥ እረፍት ጊዜዬ ውስቸጥ ስራ የምሰራ ወይም ሌሎች የእረፍት አይነቶችን የምጠቀም ከሆነ ይህ በክፍያዬ ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል?*

እንደ በአሰሪ የቀረበ የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ያሉ ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን የሚያስገኙ ስራዎችን ከሰሩ ወይም ከተቀበሉ፣ የጥቅማጥቅም ክፍያዎን እንቀንሳለን፣ ስለዚህ በሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድ ላይ የነበሩበትን የሳምንት ክፍል ብቻ ነው የሚሸፍነው።

- **በእረፍት ፈቃድ ላይ እያሉ መሥራት፡-** በሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄ መጠይቅዎ ውስጥ የሰሩዎትን ሰዓታት ሪፖርት ማድረግ አለብዎት። ምንም እንኳን ከዚያ የእረፍት ፈቃድ ባይወስዱም፣ ይህ በሁለተኛው ሥራ ላይ የተሰራውን ጊዜ ይጨምራል። ምንም እንኳን ማንኛውም ገንዘብ ባያገኙም፣ በግል ስራ ላይ የተሰሩ ሰዓታትንም ያካትታል።
- **የሚከፈልበት የእረፍት ፈቃድን መጠቀም፡-** ብዙ ሰዎች በሳምንቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ማንኛውም በአሠሪ የቀረበ የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ፣ እንደ የዕረፍት ጊዜ፣ የህመም ጊዜ፣ ወይም የበዓል ጊዜ ክፍያ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ ሪፖርት የማያደርጉበት ብቸኛው ጊዜ ቀጣሪዎ ተጨማሪ የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ (ከመደበኛው የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ የተለየ) ከሰጠ ነው። ይህ አማራጭ ለእርስዎ የሚገኝ መሆኑን አሰሪዎን ይጠይቁ።